የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ የወጣት ክንፍ ድርጅት (ኢሕአፓ ወክንድ)
Ethiopian People's Revolutionary Party Youth League (EPRP YL)

ሐምሌ 13 ቀን 2001 ዓ.ም.

July 20, 2009

## ከኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ድርጅት

## የተሰጠ መግለጫ

ስፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የተነጠቀውን ነጻነቱን፣ የተገፈፈውን መብቱን፣ የተራከሰበት አንድነቱን የተደፈረውን ሉአላዊነቱን፣ የተንቋሸሸ ስንደቁን ያስከብር ዘንድ አቋራጩ ጎዳና፣ የተባበረና የተቀናጀ ሕዝባዊ ክንድ ፣ መሆኑን ለመጠቆም ጭምር ነው ኢሕአፓ ወክንድ ብለን ምስረታችንን ያበሰርነው።

የመመስረታችን ብስራት በቀናት ቢስላ ሊጋዎች ልንባል እንችላለን። ይሁንና የብዙ ሺህ ለግላጋ ዲሞክራሲያዊያን ታጋዮች፣ ለዴሞክራሲ ደማችውን የገበሩ ሰማዕታት ተቀጥላ ነንና ነገሮችን በጥልቀት እንገነዘባለን። የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሎም የአፍሪካ ቀንድ ሁነኛ ጠላት የሆነውን የወያኔን ስርአት በሚገባ በማወቃችንም ጠንክረን ልንፋለመው መዘጋጀታችን መብታችን ብቻም ሳይሆንህ ግዳጃችን ጭምር መሆኑን በማወቅ ነው። ለዚህም ተመክሯችሁን ላጋራችሁን ድጋፋችሁን ለችራችሁን ምርቃታችሁን ላልነፈጋችሁን በሙሉ ኢወክንድ ታላቅ ምስጋናውን ያቀርባል

የወያኔ ስርአት አሸባሪ በመሆኑ በዚህ ቡድን ስር የምትተዳደር ሀገር የርሐብና የአልቂት ዜና መጨረሻና ገደብ እንደሌለው በሐገሩ ጉዳይ ባይተዋር ላልሆነ ዜጋ ሁሉ ግልጽ ነው። ይሄንን ዘግናኝ ሁኔታ ቁጭ ብለን የምንመለከተው ሳየሆን የሐገሬ ጉዳይ ያገባኛል የምንል ወጣቶች ሕዝባዊ ክንዳችንን አስተባብረን በጋራ እንድንነሳ ኢወክንድ ለመላው ኢትዮጵያዊያን ወጣቶች የትግል ጥሪ ያቀርባል።

ወያኔ ባለፉት 18 አመታት በህዝብና በሀገር ላይ የፈጸመው ወንጀ አንዳለ ሆኖ ሶስት አብይት የስሞኑ ወንጀሎችን ለመግለጽ ተገደናል።

1ኛ. ከአንድ አመት በፊት ከሁመራ እስከ ጋምቤላ ከ1600ኪ.ሜ ርዝመትና 40.ኪ.ሜ ስፋት ያለውን የኢትዮጵያን ለም መሬት ለሱዳን የሸጠው ወያኔ ዛሬ ደግሞ በኢሕአፓ የሐምሌ 3 መግለጫ እንደተመለከተው ሐምሌ 1/2001 የሱዳን ወታደሮች በኢትዮጵያ አርሶ አደሮች ላይ

ተኩስ ከፍተው ኢትዮጵያዊያንን እንደገደሉና በዚህም ድርጊት ወያኔ ቀጥተኛ ተባባሪነቱን በድጋሚ ማሳየቱ ስናይ፣

2ኛ. ባሳለፍነው ሁለት ሳምንት በወርሐ ሰኔ አጋማሽ ወያኔ በካድሬዎቹ አማካይነት በቆሰቆሰው የሐይማኖት ግጭት እንደ ገላጋይ ገብቶ ተኩስ በመክፈት በደሴ ያፈሰሰው የዜጎች ደም ስንመለከት፣

3ኛ. የፀረ ሽብርተኛ አዋጅ ብሎ እጃችውን ብቻ እንዲስቅሉ በተቀመጡ የፓርላማ አባላቱ ያፀደቀው ህግና የአባቶችና የእናቶች የተጋድሎ ውጤት ያፈራውን የሐገሪቱን ሰንደቅ አላማ በማን አለብኝና በእብሪት ተወጥሮ ሊቀይር መነሳቱን ስንስማ፣

ኢወክንድ ጅቡ ከሚበላህ በልተህው ተቀደስ የሚለውን የማሳሰቢያና የማስጠንቂያ መልእክት እያስተላለፈ የሚከተለውን ጥሪ ያቀርባል።

Tel 202-291-5832 P.O.Box 56068 Washington DC 20040 e-mail: join@eprpy.com
www.eprpy.com

ሀ. ዋቢ ጠበቃ የሌላችሁ አርሶ አደሮቻችን ለሱዳን ከነ መሬታችሁ ተቸራችሁ በውርደት አንገዛም በማለት የምታደርጉትን የሞት ሽረት ትግል ለማገዝ ኢወክንድ ከጎናችሁ መስለፉን እየገለጸ በጎንደርና በተጎራባች ክ/ሐገራት የሚገኙም የኢወክንድ አባላት ተገቢውን እገዛ እንዲያደርጉ ጥሪውን ያስተላልፋል።

ለ. ከህብረ ብሔራዊነት አልፎ ህብረ ሃይማኖትነታዊ መሆኗን ታሪክ የመስከረላት ኢትዮጵያ በዋቢነትና በግንባር ቀደምትነት ሁለቱ ሃይማኖቶች በእኩልነት ተፋቅረውና ተከባብረው ከሚኖሩባት የሀገራችን ክፍል ውስጥ አንዷ ወሎ ነች። ዛሬ ይህንን በጋራ ተዋዶና ተከባብሮ የሚኖር ሕዝባችንን መሰረት ሊንድ የሚችል ምድራዊ ሐይል ባይኖርም ወያኔ ደም ለማፋሰስ የሚያደርገውን ሙከራ በፅናት ከሕዝባችን ጎን ቆመን መመከት እንዳለብን ለሀገራችን ወጣቶች ጥሪ እናቀርባለን።

ሐ. ትላንት ጨርቃችሁን ማንጠልጠል ትችላላሁ ብሎ በክቡር ሰንደቃላማችን ላይ የተሳለቀው ወያኔ አልፎም ከጨርቁ ሳይሆን ከበስተጀርባው ባለው መልእክት ላይ ነው ፅባችን ያለን ወያኔ የሐገሪቱን ስንደቅ አላማ ሐገር ሊያፈርስበት በተነሳበት አርማ ሊተካው አዋጅ ማስነገሩ የኢትዮጵያ ወጣቶች በጭራሽ የማንቀበለውና ይበልጥ የኢትዮጵያን ስንደቅ ከፍ አድርገን የምንታይበት ወቅት በመሆኑን በመገንዘብ የኢትዮያዊነት ምልክት የሆነውን ከትውልድ ትውልድ የተላለፈልንን ሰንደቅ ዓላማ ከምንግዜውም በላይ እንድናውለበልብ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥሪ እናቀርባለን።

**ኢወክንድ**

**የኢትዮጵያ ወጣቶች የትግል ገድል ታሪክ ዛሬም ህያው ነው!!!**

**እናቸንፋለን!!!**

Tel 202-291-5832 P.O.Box 56068 Washington DC 20040 e-mail: join@eprpy.com
www.eprpy.com